# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አማራጭ የሙግት አፈታት ዘዴዎች

በካፒታል ገበያ አዋጅ መውጣትን ተከትሎ የአፈፃፀም መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ መደረጋቸው የረጅም ጊዜ ካፒታልን ለመሰብሰብ እና የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማነቃቃት ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ሆኖም ግን የማንኛውም የካፒታል ገበያ ውጤታማነት እና ተዓማኒነት የሚመዘነው ለኢንቨስተሮች ከሚሰጠው ጥበቃ አንፃር ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሆነ አማራጭ የሙግት አፈታት ሥርዓት ማለትም ሽምግልና እና የግልግል ዳኝነት ለገበያው ተዓማኒነት ወሳኝ አስተዋፅዖ አላቸው።

ሽምግልና ተከራካሪ ወገኖች ገለልተኛ በሆኑ አስታራቂ ሰዎች እየታገዙ እንዲደራደሩ፣ እንዲግባቡ እና ከስምምነት ላይ እንዲደርሱ የሚደረግበት ሂደት ሲሆን የግልግል ዳኝነት ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች ግጭታቸውን ለገለልተኛ የግልግል ዳኛ በማቅረብ የሚስማሙበት ሂደት ነው። በግልግል ዳኝነት ሂደት የግልግል ዳኞች ውሳኔ ልክ እንደ መደበኛ ፍርድ ቤት ፍርድ አስገዳጅ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ አለ።

ይህ አማራጭ የግጭት አፈታት ሥርዓት በአዋጁ አንቀጽ 64 እና ተከታዮቹ መሰረት ከተቋቋመው እና በባለስልጣኑ ወይም የባለስልጣኑን ተግባርና ኃላፊነት በሚያስፈጽሙ ሰዎች የተላለፉ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በይግባኝ ከሚያየው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት የሚለይ ነው።

በስልጣን ረገድ ሰንመለከት አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ያለው ሲሆን ከግብይት ማገድ፣ የገንዘብ ቅጣት፣ ፈቃድ መሰረዝ፣ከምዝገባ መሰረዝ እና መሰል አስተዳደራዊ ቅጣቶች ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን በመመርመር አስገዳጅ ውሳኔ የሚሰጥ ተቋም ነው።

ይህም ሥርዓት አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የስልጣን አጠቃቀም ላይ ገለልተኛ ፍተሻ እንዲያደርግ በማስቻል ተጠያቂነትን እና ተገቢነትን ያረጋግጣል። የፍርድ ቤቱን ሚና በተመለከተ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ በተጻፉ ጽሑፎች የተዳሰሰ በመሆኑ በዚህ ጽሑፍ ትኩረታችንን በአማራጭ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ላይ እናደርጋለን።

ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ የተካተቱትን አማራጭ የሙግት አፈታት ዘዴዎችን ትንተና ያቀርባል። በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና ተዛማጅ ሕጎች ባለ ብዙ ደረጃ የግጭት አፈታት መዋቅር ያሉ ዘዴዎችን ይመረምራል። በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በኩል የሚደረጉ የግልግል ዳኝነት እና የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሚናዎችን ይገመግማል።

# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አማራጭ የሙግት አፈታት ዘዴዎች

## 1. በካፒታል ገበያ አማራጭ የሙግት አፈታት አስፈላጊነት

አማራጭ የሙግት አፈታት ዘዴዎች ከፍተኛ የኢንቨስተር ጥበቃን ለማረጋገጥ እና የገበያ እምነትን ለማጠናከር ዋና መሠረት ናቸው።ኢንቨስተሮች በካፒታል ገበያ ላይ ያላቸው እምነት ጠንካራ መሆን ዘርፉ የሚያንቀሳቅሰው ገንዘብ እንዲያድግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ይህ እምነት በገበያው የሚፈጸሙ ጥፋቶች እና ስህተቶች ወዲያውኑ እርምት ካልተወሰደባቸው እና አለመግባባቶች በተራዘመ የሙግት ሂደት ውስጥ የሚያልፉ ከሆነ ሊሸረሸር ይችላል።

የሙግት አፈታት ዘዴዎች የገበያ ተዓማኒነት ምሰሶ ሲሆኑ ሁለት ዓላማ አላቸው። በመጀመሪያ ደረጃ የማስተካከያ መፍትሄ የመስጠት ሚና ያላቸው ሆኖ ለተበደሉ ወገኖች ለኢንቨስተሮች፣ ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች ወይም ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች የማስተካከያ እና የካሳ አማራጮችን የሚያቀርቡ ናቸው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከተገበያዮች የሚጠበቁ የሥነ-ምግባር ደረጃዎችን ይቀርፃሉ፣ ያብራራሉ፣ ተጥሰው ሲገኙ ውጤቶችን በማስቀመጥ የማጭበርበር እና የማታለል ድርጊቶችን ይከላከላሉ።

የሽምግልና እና የግልግል ዳኝነት አስፈላጊነት ሌላኛው ምክንያት ዳኞቹ የተለያየ ሙያ ስብጥር ያላቸው መሆኑ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በህግ፣ በካፒታል ገበያ፣ በኢኮኖሚክስ ወይም በፋይናንስ በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ ያላቸው እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ይህም ውሳኔ ሰጪዎች የክርክሩን አውድ እንዲረዱ በማድረግ ሂደት እና ትክክለኛ ፍትህን ከማረጋገጥ አንጻር የራሱን ሚና ይጫወታል።

እነዚህ አማራጭ ዘዴዎች ክርክሮች በዘርፉ ቀጥተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲፈቱ በማድረግ ፈጣን መፍትሔ የሚሰጡ ናቸው። ይህም በተጓዳኝ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ቢታይ ኖሮ ሊፈጠር የሚችለውን መጨናነቅ የሚቀንስ ከመሆኑ ባሻገር ውስብስብ በሆኑ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጉዳዮች በዘርፉ በቂ ልምድ በሌላቸው መደበኛ ፍርድ ቤቶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ይከላከላል።

በተጨማሪ በፍርድ ቤት ሂደት ከመግባት በፊት እነዚህን አማራጭ ዘዴዎች መጠቀም የጊዜና የወጪ ቅነሳ ጥቅም ያለው እንዲሁም የኢንቨስተር እምነትን ይጠናክራል። ለካፒታል ገበያ ግጭት አፈታት ተብሎ ራሱን የቻለ የሽምግልና እና የግልግል ዳኝነት ተደራሽ በሆነ መልኩ መዘረጋቱ የኢንቨስተሮችን መብት ጥበቃ ቁርጠኝነት የሚያሳይ በመሆኑ የገበያ ተሳትፎን ያበረታታል።

## 2. ቁልፍ ህጎች እና የአስተዳደር መርሆዎች

የክርክር መፍትሄ ሥነ-ምህዳር የተገነባው በህግ መሳሪያዎች ተዋረድ ላይ ነው፡

የካፒታል ገበያ አዋጅ እና መመሪያዎች፡ በዋናነት ከያዝነው ጉዳይ ጋር በተያያዘ በአዋጁ አንቀጽ 111(4) መሰረት በባለሥልጣኑ እንደሚወጣ የሚጠበቀው የግልግል ዳኝት ግጭት አፈታት ሥርዓት መመሪያ ይገኝበታል። በካፒታል ገበያ አዋጅ መሠረት በገበያ ተዋንያን መካከል የሚነሱ የሲቪል አለመግባባቶች በመጀመሪያ ወደ ሽምግልና ይመራሉ።

# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አማራጭ የሙግት አፈታት ዘዴዎች

ዓላማው ወደ መደበኛ ሙግት ሳይሄዱ በውይይት እንዲፈቱ ለማበረታታት ነው። ሽምግልና ካልተሳካ፣ ክርክሩ በግልግል ዳኝነት መፈታት አለበት፣ ይህም አስገዳጅ እና ተፈጻሚነት ያለው ውጤት ያረጋግጣል። የግልግል ዳኝነት ውሳኔው አንዴ ከወጣ በኋላ የመጨረሻ አስገዳጅ ሲሆን፣ ይግባኝ የሚፈቀደው በፍትሃብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት በተደነገጉት ውስን ሁኔታዎች ብቻ ነው። ፍትሃዊነትንና ወጥነትን ለመጠበቅ፣ ባለሥልጣኑ የግልግል ዳኞችን ብቃትና ሹመት፣ በግልግል ዳኝነት ወቅት መከተል ያለባቸውን ሂደቶች እና የግልግል ዳኞችን ወጪዎች ምደባ የሚመሩ መመሪያዎችን እንዲያወጣ ሥልጣን ተሰጥቶታል። በዚህ መንገድ፣ አዋጁ ቅልጥፍናን፣ የባለሀብቶችን ጥበቃ እና የገበያ ተማኝነትን ቅድሚያ የሚሰጥ የክርክር አፈታት ግልጽ፣ የተዋቀረ መንገድ ያስቀምጣል።

ከዚህ መመሪያ በተጨማሪ ሌሎቹ በአዋጁ አንቀጽ 108(2) መሰረት በባለስልጣኑ ለአዋጁ አፈጻጸም አስፈላጊ ናቸው ተብለው የወጡ መመሪያዎች ለግጭት አፈታት ሥርዓት የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ። እነዚህ መመሪያዎች ለግጭት አፈታት ቁልፍ መሳሪያ በመሆን የሚያገለግሉ ብቻ ሳይሆኑ መሠረታዊ መብት እና ግዴታዎችን ያቋቁማሉ። የእነዚህ መብት እና ግዴታዎች መጣስ አለመግባባቶችን በማስከተል ወደ ግጭት አፈታት ሥርዓት ያመራል።

የግልግል ዳኝነትን እና የእርቅ አሠራር ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁ.1237/2013፡- ባለሥልጣኑ በካፒታል ገበያ አዋጅ መሰረት ሽምግልና እና የግልግል ዳኝነት አሰራርን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 111(4) መመሪያ ማውጣት ይጠበቅበታል። በዚህ ረገድ በካፒታል ገበያ ተዋንያን መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በኩል በራሱ ወይም በአስተባባሪነት በሚከናወን ሽምግልና በመጀመሪያ ደረጃ በገበያው የሚታይ ሲሆን በገበያው መተዳደሪያ ደንብ ስለሽምግልና በተመለከቱ ደንቦች እና ሁኔታዎች መሰረት ውሳኔ የሚሰጠው ይሆናል። በሽምግልናው ተከራካሪ ወገኖች በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ወይም እልባት ማግኘት ካልተቻለ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥበት አሰራር በገበያው የውስጠ ደንብ ተመልክቷል።

ከዚህ በተጨማሪ ገበያው ራሱ የክርክሩ አካል ሲሆን ጉዳዩ በቀጥታ በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ዳኝነት ኢንስቲትዩት ወይም በኢትዮጵያ የማስማማትና የግልግል ዳኝነት ይታያል።

በዚህ ሂደት የግልግል ዳኝነቱን የሚመራው አካል በገበያው መተዳደሪያ ደንብ የተመለከቱ የግልግል ዳኝነት ድንጋጌዎችን እንዲሁም በዛ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲኖሩ እንደሁኔታው በግልግል ዳኝነት አዋጁ እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ስለ ግልግል ዳኝነት የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ተፈጻሚ ያደርጋል።

የግጭት አፈታት የህግ ማዕቀፍ የሚመራባቸው መሰረታዊ መርሆዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ።

የኢንቨስተሮች ጥበቃ፡ የሁሉም የካፒታል ገበያ የግጭትአፈታት መመሪያዎች እና ውስጠ ደንቦች ዋነኛ አላማ የኢንቨስተር ጥበቃ በመሆኑ የመመሪያዎች እና ደንቦች ትርጓሜ ከዚህ አንጻር መታየት ይገባል።

የተቆጣጣሪ አካል ስልጣን፡ መዘንጋት የሌለበት በዚህ ሂደት ጉዳዩ ወደ ግልግል ዳኝነት ወይም እርቅ የሚሄድ ቢሆንም ባለሥልጣኑ ተቆጣጣሪ ተቋም እንደ መሆኑ ጉዳዮችን የመመርመር፣ የአስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመውሰድ እና የማስፈጸም ዋነኛ ሥልጣን አለው።

የሽምግልና እና የግልግል ዳኝነት አስገዳጅነት፡ በካፒታል ገበያ ተዋንያን መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በተለይ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ በአጠቃላይ በመጀመሪያ በግልግል ዳኝነት በኩል ማለፉ አፋጣኝ መፍትሄ ከማግኘት አንጻር የማይተካ ሚና የሚጫወት ነው።

# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አማራጭ የሙግት አፈታት ዘዴዎች

ባለሙያ፡ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይቶች አለመግባባቶች ውስብስብ የፋይናንስ፣ የቁጥጥር እና የቴክኒክ ጉዳዮችን የሚያካትቱ በመሆናቸው በዘርፉ የተለየ እውቀት እና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች መታየታቸው ትክክለኛ ፍትህን ከማስፈን አንፃር ጉልህ ድርሻ አላቸው።

## 3. የካፒታል ገበያ የሽምግልና እና የግልግል ዳኝነት ሥርዓት

እንደ ተከራካሪ ወገኖች ስምምነት የሽምግልና እና የግልግል ዳኝነት በሚከተሉት ላይ የመጀመሪያ ወይም የመጨረሻ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ስልጣን ሊኖረው ይችላል። የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በሚያስተባብረው ሽምግልና እና የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ዳኝነት ኢንስቲትዩት ወይም የኢትዮጵያ የማስማማትና የግልግል ዳኝነት ማዕከል በሚያከናወነው የዳኝነት ሥራ ከሚታዩ ጉዳዮች መካከል ሁሉንም አይነት ገንዘብ ነክ ክርክሮች በተለይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የሚከናወኑ ግብይቶች ጋር በተያያዘ በግብይት ፈጻሚዎች አባላት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፤በገበያው አባላት እና በደንበኞቻቸው መካከል የሚነሱ ክርክሮች፤ በራሱ በገበያው እና በአባላት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ይገኙበታል።

ከዚህ በተጨማሪ ክርክሩ ራሱ ገበያውን የሚያካትት ሲሆን ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ተቃራኒ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር ጉዳዩ በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ዳኝነት ኢንስቲትዩት ወይም በኢትዮጵያ የማስማማትና የግልግል ዳኝነት ማዕከል መታየት የሚችልበት ሥርዓት ተዘርግቷል።

በዚህ ሂደት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ ባላቸው የግብይት ፈጻሚ አባላት መካከል ወይም በግብይት ፈጻሚ አባላትና በራሱ በገበያው መካከል የሚነሱ የፍትሐብሔር አለመግባባቶች በሽምግልና በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ሊፈቱ የማይችሉ ከሆነ በግልግል ዳኝነት ሊፈቱ እንደሚገባ በገበያው መተዳደሪያ ደንብ ተመልክቶ ይገኛል፡

## 4. የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሚና

ምንም እንኳን መደበኛ ፍርድ ቤቶች በማዕቀፉ ያላቸው ሚና የተገደበ ቢሆንም የካፒታል ገበያ ጉዳዮችን በይግባኝ ሊያዩ የሚችሉበት አግባብ በአዋጁ ተመልክቷል።

የካፒታል ገበያ አዋጅ አንቀጽ 67(2) የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሕግ ስህተት ምክንያት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለቀርብበት እንደሚችል ይደነግጋል። ከዚህ በተጨማሪ በሽምግልና እና የግልግል ዳኝነት አካላት የሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች ለማስፈጸም እና የእግድ ትዕዛዞችን ለማውጣት የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን መጠቀም አስፈላጊ ነው።

# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አማራጭ የሙግት አፈታት ዘዴዎች

## 5. ማጠቃለያ

በካፒታል ገበያ አዋጁ እና መመሪያዎች ውስጥ ባለ ብዙ አማራጭ የሙግት አፈታት ዘዴዎች ተካተው ይገኛሉ፡፡ በሙግት አፈታቱ ሥርዓት የሚታየው ገንዘብ ነክ ጉዳይ ሲሆን በገበያው እና በሌሎች ከላይ በተጠቀሱ ተቋማት የሚመራው የሽምግልና እና የግልግል ዳኝነት የህግ ማዕቀፍ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ ጉዳዮቹ በባለሙያዎች የሚታዩ ከመሆኑ አንጻር ቅልጥፍና እና ጥራትን በማስጠበቅ የኢንቨስተሩን እምነት የሚያጎለብቱ ናቸው፡፡ እነዚህ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ብቻ ሳይሆኑ የገበያ ተዓማኒነት ምሶሶዎች እና የኢንቨስተሮች በራስ መተማመን እውነተኛ ጠባቂዎች ናቸው፡፡
የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት፣ የሙግት አፈታት ተቋማት፣ ባለሥልጣኑ እና ገበያውን ጨምሮ ሌሎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች በካፒታል ገበያ ተዋንያን ላይ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን እና የሚወሰዱ እርምጃዎችን ለህዝብ ይፋ በማድረግ የግብይት ሥነ-ምግባርን በመቅረጽ እና ግልጽነትን በማስፈን የገበያው ተዓማኒነትን ለማጎልበት በጋራ እና በተናጠል የየራሳቸውን ሚና ልንጫወት ይገባል፡፡